በአዲስ አበባም ብዙ ተማሪዎች የወታደር መንግስት የኢትዮጵያን ችግር ሊፈታ አይችልም፡ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም በማለት ሰልፉን በማከታተል ሰልፍ አድርገዋል::ብዙዎች ተደብድበዋል፣ ቆስለዋል፣ ታስረዋል፣ የታሰሩት ተማሪዎች ምን ያህል እንደሆነ በእርግጥ አልታወቀም::ትግሉ ግን በየቦታው እየቀጠለ ነው::

ከሻምበል ደምሴ ተፈሪ ጋር በርከት ያሉ የክብርዘበኛ አባሎች /ምናልባት የጉሉስ ደርጉ አባሎች በሙሉ/ መያዛቸውና መታሰራቸው ይወራል:: ደርጉ ሻምበሉን አሳልፎ ቢሰጥም እርሱም ሆነ ጓደኞቹ የወታደርን መንግስት የሚያወግዙና የሕዝብ መንግስት እንዲቋቋም ደጋግመው እንደ ጠየቁ የአደባባይ ምስጢር ነው፣ ከአብዮታዊነት በጣም የራቁ ነው::

የምድር ጦር መሃንዲስና የአርሚአቪዬሽን አባሎች ከስድስት መቶ ባላይ የሚሆኑ በጅምላ መታሰራቸው ቀደም ብሎ ታውቋል:: አንዳንዱ ገንባር ቀደሞቹን በጨለማ ቤት ውስጥ ይዘው በማሰቃየት ላይ ሲሆኑ አብዛኞቹን ግን ወደሀለታ ወስደው አሰረዋቸዋል::ይህ ሁሉ የወታደር መንግስትን በመቃወም ሕዝባዊ መንግስት እንዲቋቋም ፊትለፊት በመጋፈጣቸው ነው፣ የትግሉ ግንባር ቀደም በመሆናቸው ነው::

በየክፍለ ሃገሩና በየአውራጃው የወታደሩን መንግስት በመቃወም፡ የሕዝብ መንግስት ይቋቋም በማለት ድምፃቸውን ያሰሙ የነቁ ተራማጆች እየታፈኑ ናቸው:: በሲዳሞ በሃረርጌና በሌሎችም ክፍለ ሃገሮች በርከት ያሉ ሰዎች ታስረዋል፣ ቁጥራቸውና ሁኔታቸው ገና በደንብ አልታወቀም::